www.ethiotelecom.et
P.O. Box 1047 Addis Ababa Ethiopia
tel.: +251 (0) 115 505 678
fax: +251 (0) 115 515 777

# የጨረታ ማስታወቂያ

**ጨረታው የሚጀመርበት ቀን፡ ጥር 14 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ጨረታው የሚጠናቀቅበት ቀን፡ የካቲት 05 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ጨረታው የሚከፈትበት ቀን፡ የካቲት 06 ቀን 2010 ዓ.ም**

ኢትዮ ቴሌኮም ያገለገሉ የቢሮ ዕቃዎች፤ የቤት መገልገያ ቁሳቁስ፤ የግንባታ ግብኣት ማምረቻ ማሽኖች እና ሌሎች የተለያዩ ዓይነት ያገለገሉ ንብረቶችን ባሉበት ሁኔታ በዝግ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል።

1. ስለ አሻሻጡ የሚገልፅ ዝርዝር የጨረታ መወዳደሪያ ሰነዱን ተጫራቾች ከጥር 14 እስከ የካቲት 05 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 10:00 ድረስ በኢትዮ ቴሌኮም ዋናው መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 214 ዘወትር በሥራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100.00 ከፍለው በመውሰድ በጨረታው ላይ መሳተፍ ይችላሉ።
2. ንብረቶቹን ለማየት ለሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የገዙበትን ደረሰኝ በመያዝ መስቀል ፍላወር አካባቢ በሚገኘው ኢትዮ ቴሌኮም ዕቃ ግምጃ ቤት በመገኘት ከጥር 14 እስከ የካቲት 05 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ቀኑ 06:00 ሰዓት ድረስ ማየት ይችላሉ።
3. ተጫራቾች በጨረታዉ ለመሳተፍ ውጤቱ እንደታወቀ የሚመለስ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለመግዛት የሚያቀርቡበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% (አስር ከመቶ) ማስያዝ ይኖርባቸዋል። የጨረታ ማስከበሪያ ከታወቀ ባንክ ተረጋግጦ በሚቀርብ ሲፒኦ (CPO) መሆን አለበት።
4. ተጫራቾች ለመግዛት የሚፈልጉትን ንብረቶች የሚገዙበትን ዋጋ በጨረታ ሰነዱ ላይ በሚቀመጠዉ ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ/ ፎርም መሰረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
5. ጨረታዉ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት በዋና መ/ቤት የካቲት 06 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 05:00 ሰዓት ይከፈታል።

**የጨረታውን ዝርዝር መረጃ ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይችላሉ።**

**ኢትዮ ቴሌኮም**